# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

**የዓቢይ ጾም ስምንተኛው ሰንበት «ሆሳዕና» ይባላል።**

በዚህ ዕለት የሚፈጸመው ሥርዓተ አምልኮ ከዜማው እስከ ስርሆተ ሕዝብ (ቅዳሴ አልቆ ሥርዓተ አምልኮው እስከሚከናወንበት ወቅትና ሰዓት ድረስ) ከሌሎች ሰንበታት ይልቅ የሰፋና የረዘመ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐተ
በእንተ ጸላኢ
ከመትንሥቶ ለጸላኢ ወለገፋኢ

ከሕጻናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ
ስለ ጠላትህ
ጠላትና ቂመኛን ለማጥፋት
መዝ ፰፥፪

ትርጉም፥
ከሕጻናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህልኝ
ጸላኢ ገፋኢ የሚሆን ዲያቢሎስ ደስ አይበለው ብለህ
ጸላኢ ገፋኢ የሚሆን ዲያቢሎስን ትረታው ዘንድ

ወንጌል፥ ዮሐ ፭፥፲፩፥፲፫
ቅዳሴ፥ የጎርጎሪዮስ ቅዳሴ

## የዕለቱ ትምህርት

## ሆሳዕና

በዚህ ዕለት መሲህ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ የተዘመረው መዝሙር «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሳዕና በአርያም» የሚል ነበር። በአጠቃላይ የዕለቱ ወንጌል ታሪክ እንደዚህ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀመዛሙርቱ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ደብረ ዘይት ተራራ ላይ ወደምትገኝ ቤተፋጌ ከምትባል ሥፍራ ደረሱ። («ኢየሩሳሌም» ማለት «የሰላም ከተማ» ማለት ሲሆን «ቤተፋጌ» ማለት ደግሞ የበለስ ቤት ማለት ነው። በእኛ አባቶች ደግሞ «የተመሳቀለ ጎዳና ተብሎ ተተርጉሞአል።) ጌታችንም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን «በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ የታሰረች አህያ ከውርንጭላዋ ጋር ታገኛላችሁ ፈትታችሁ አምጡልኝ ማንም አንዳች ቢላችሁ «ለጌታ ያስፈልጉታል» በሉ አላቸው። ሐዋርያትም ፈትተው አመጡለት። (የሐዋርያት አገልግሎት የታሰሩትን በወንጌል ቃል መፍታት ነው። ሌቦች አጋንንት ያሰሩዋቸው ብዙ የኃጢአት እስረኞች አሉ። ጌታ

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፱፥፲፩ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፬፥፩-፲፪ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፰፥፲፩-፳፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

የታሰሩትን እንዲፈቱ ተማሪዎቹን አዟቸዋል። በሐዋርያት አገልግሎት የተፈቱትም የመሲሁ መገለጫዎች የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ይሆናሉ።) በትንቢተ ዘካርያስ ፱፥፱ የተነገረው የትንቢት ቃል ይፈጸም ዘንድ ጌታ በአህያይቱና በውርንጭላዋ ላይ ይቀመጥ ዘንድ ሐዋርያት በአህያይቱ ጀርባ ላይ አነጠፉለት። የዓለምን ኃጢአት የሚጋርድ አዲስ ልብስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ልብሰ ሃፍረትን እንደሚጋርድ ከባቴ አበሳ በደልን የምትጋርድ ነህ ሲሉ ነው ልብስ ያነጠፉለት። ጌታም ተቀመጠባቸው።

<u>አህያ</u>፥ የተናቀች ናት። ራሳቸውን ዝቅ ባደረጉ የተሰበረ መንፈሳቸው ወደ አምላክ እንደሚመለከት ያስተምራል (ኢሣ ፶፫፥፳፫ ። ማቴ ፲፩፥፳፱ ። መዝ ፶፥፲፯-፲፰)። ሕዝቡም ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ (እንኳን አንተ የተቀመጥክባት አህያ እንኳ ትቢያ ሊነካት አይገባም ሲሉ ይላሉ አባቶች) ለንጉሥ የሚገባውን አክብሮት መግለጻቸው ነው (፩ኛ ነገ ፱፥፲፫) «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ ሆሳዕና በአርያም« በማለት መዘመር ጀመሩ።

ሆሳዕና፥ ማለት አሁን አድን ማለት ነው። በዳዊት መዝሙር ቃሉ ተጠቅሷል። «አ እግዚአ አድህንሶ - አቤቱ አሁን አድን» ተብሎ እንደተጻፈ። (መዝ ፻፲፯፥፳፭)

በአርያም፥ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነውን ሰማይ ያመለክታል። በመሆኑም በሰማይ ያለ በሰማይ የሚኖር ሰማያዊ የሆንህ መድኃኒት ሆይ አሁን አድን እያሉ ዘመሩ።

ጩኸታቸው በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል። የመጀመሪያው ከሮማውያን ቅኝ አገዛዝ አድን የሚል የሥጋ ጩኸት ሲሆን ሁለተኛው (ይህ ዋነኛው ሲሆን) ከሞተ ሥጋ ከሞተ ነፍስ አድን ማለታቸው ነበር። ሌላው በምስጋናቸው ውስጥ የተካተተው ቃል «የዳዊት ልጅ» የሚል ሲሆን እርሱ መሲሁ መሆኑን ሕዝቡ እንደተገነዘቡ ያመለክተናል (ማቴ ፲፪፥፳፫ ፡፡ ፳፥፳፫ ፡፡ ፳፥፴ ፡፡ ፳፪፥፵፪ ፡፡ ፱፥፪)።

«የአባታችን የዳዊት መንግሥት» ማለታችን ለዳዊት የተሰጠው የተስፋ ቃል መፈጸሙን ያመለክታል። የእስራኤል መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥት ነበረች። የሰው ሁሉ ገዢ እግዚአብሔር ስለሆነ ከአዳም እስከ ሳሙኤል ሕዝቡን የሚያዝ የሚመራ በተስፋው የዘር ሐረግ ውስጥ ባለቤቱ እግዚአብሔር በመሆኑ ንጉሥ አልነበረም። በሳሙኤል ጊዜ ግን ሕዝበ እስራኤል እንደ አሕዛብ ንጉሥ ፈለጉና ንጉሥ አንግስልን ብለው ሳሙኤልን ጠየቁት። ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት አንተን ሳይሆን እኔን ነውና የናቁት አንግስላቸው አለው። ሳሙኤልም ንጉሣችን እግዚአብሔር ስለሆነ ይቅርባችሁ ቢላቸው እንቢ ስላሉት አህያ ጠባቂውን ሳኦልን ሾመላቸው። እግዚአብሔር እንዲገዛው ያልወደደን ሕዝብ የአህያ እረኛ ይገዛዋል።

የሳኦልም መንግሥት ተሻረና እግዚአብሔር ሳኦል እያለ እንደፈቃዱ ሕዝቡን የሚመራበትን የእርሱ መንግሥት የምትገለጥበትን ዳዊትን እንዲቀባ አደረገ። የዳዊት መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥት ነበረች። ለዳዊትም ከአብራክህ የሚከፈለው ልጅህ በዙፋንህ ላይ ይቀመጣል ብሎ ለጊዜው ለሰሎሞን ሲሆን ፍጻሜው ግን ጌታ ከእርሱ እንደሚወለድ ቃል ገብቶለት ነበር። መበስር መልአክ ቅዱስ ገብርኤልም ይህንኑ ተናግሯል (ሉቃ ፩፥፴፫)። ስለዚህ በስውር ትተላለፍ የነበረው የእግዚአብሔር መንግሥት በእግዚአብሔር ልጅ መወለድ ስለተገለጠች የአባታችን የዳዊት መንግሥት በማለት ዘመሩ። በዚህ ሁኔታ መሲህ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ መላው ከተማ «ይኼ ማን ነው?» ብሎ ተናወጠ። ሕዝቡም «ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣው ነቢዩ ኢየሱስ ነው» አሉ። ከዚህም በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ የንግድ ማዕከል የነበረውን ቤተ መቅደስ ከንግድና በንግድ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች አጸዳ። ቤቴ የጸሎት ቤት እንጂ የንግድ ቤት አይደለም ብሎ በግልጽ ተናገረ። በቤተ መቅደስ የነበሩትን እውራን ዓይን አበራ።

ሸባዎችን እረታ፤ ጎባጣዎችን አቀና፤ ለምጻሞችን አነጻ። ነገር ግን ቤተ መቅደሱን ያዙበት የነበሩት የጸሎት ቤቱን የወንበዴ ዋሻ ያደረጉት የአእምሮ እውራን ሳይበራላቸው ቀረ። ሰንኩል አመለካከታቸውም ሳይቀና ቀረ። በመሆኑም «ሆሳዕና» ብሎ የዘመረውን ሕዝብ አጠጣው «ዓርብ» ይሰቀል እንዲል አደገሩት።

መድኃኒታችን በቤተ መቅደስ እንዳለ በቤተ መቅደስ የነበሩ ሕጻናት መዝሙር ጀመሩ ተማሪዎቹም አብረው «ሆሳዕና» ሲሉ የካህናት አለቆች ዓይናቸው ደም ለበሰ፤ ልባቸው በቁጣ ተሞላ። «የሚሉትን አትሰማም ወይ ዝም በሉ በላቸው» አሉት ጌታን። ጌታ «እነርሱ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይዘምራሉ፤ በዚያውስ ላይ በዳዊት መዝሙር «ለሚጠቡ ሕጻናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህልኝ ጠላት ዲያቢሎስ ደስ አይበለው ብለህ» ተብሎ የተጻፈውን አታስተውሉምን?» አላቸው (መዝ ፰፥፪)።

ባለ አእምሮ ነን የሚሉት ልብ ሲታወር አንደበታቸው በሰይጣን ምክር ሲዘጋ የሕጻናት አንደበት ምስጋናን ያዘንብ ነበር።

አንባቢ ሆይ፥ እንደ ሐዋርያት ታዛዥ ልብ ይኖርህ ዘንድ እግዚአብሔርም እስራትህን ይፈታልህ ዘንድ ጸልይ። የተናቀችውን ፍጥረት እንዳልናቀ ምንም ኃጢአተኞች ብንሆን በንስሃ ወደ እርሱ ብንቀርብ እንደሚቀበለን እወቅ።

አንዳንድ ሰዎች ክብርን ይፈልጋሉ አያገኙትም፤ ትልቅ መባል በሕዝብ ዘንድ መወደድ ይፈልጋሉ አይሆንላቸውም፤ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? የክርስቶስ ማደሪያዎች ስላልሆኑ ነው። ነገር ግን በዛሬው ታሪክ የመሲሁ መቀመጫ የሆነች አህያ በምትረግጠው ምድር ላይ ጨርቅ ሲነጠፍላት ቅጠል ሲጐዘጐዝላት አየን። አዎ! የመሲህ ክርስቶስ ማደሪያ የሆኑ ሁሉ ክብር አላቸው። በራሳቸው ለመክበር የሚፈልጉ ግን ክብርን አያገኙም። የክብር ባለቤት ክርስቶስ ያደረባቸው መንፈሳቸው የተሰበረ ቅዱሳን ግን ክብር አላቸው፤ እናከብራቸውማለን። እርሱ የቅዱሳን ክብር ነውና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።